# ኢትዮጵያዊያን እስላሞችና እጅግ አሳሳቢው የኢትዮጵያዊነት ስሜታቸው!

ትናንትና ሰኔ **30 2008** ዓ.ም. የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚንስትር ቤንጃሚን ኔታኒያሁ ከሌሎች የመንግሥታቸው ባለሥልጣናትና የሀገራቸው ባለሀብቶች ጋር በመሆን ሀገራችንን መጎብኘታቸው ይታወቃል፡፡ ይሄንን ጉብኝት ተከትሎ ኢትዮጵያዊያን የእስልምና ተከታዮች እየሰጡት ያለው ምላሽ እጅግ አስገርሞኛል፡፡ እነዚህ ወገኖች ጉዳዩን እያዩት ያለው እንደ አንድ ዓረብ እንጅ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ከሀገርና ከሕዝብ ጥቅም አንጻር አለመሆኑ እንዴት**?** እና ለምን**?** አሰኝቶኛል፡፡

በእርግጥ ይሄ የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግር በከፊል የእስልምና ተከታይ ወገኖቻችን ላይ ሲስተዋል ይሄ የመጀመሪያው አይደለም፡፡ ከጥንት ጀምሮ ያለ ችግራቸው ነው፡፡ በግራኝ አሕመድና በደርቡሽ ዘመን የታየና ታሪክ ዘግቦ የያዘው ክስተት ነው፡፡ ይሄ ያልተገባና እጅግ ቂልነት የተሞላ አስተሳሰብን በመያዝ እነኝህ ወገኖቻችንን ከሌሎች ሀገራት እስላሞች የሚለያቸውና ብቸኛም የሚያደርጋቸው አስተሳሰብ ነው፡፡ የሌሎች ሀገራት እስላሞች የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ጥቅም ያስቀድማሉ፡፡ ለእምነታቸው መቆም ካለባቸው ከሀገራቸውና ከሕዝባቸው ጥቅም በኋላ የሚያስቡበት እንጅ የፈለገ ቢሆን እምነታቸውን ምክንያት አድርገው እንደኛዎቹ ሁሉ የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ጥቅም አሳልፈው በመስጠት በገዛ ሀገራቸውና ሕዝባቸው ክህደት ሲፈጽሙ አይስተዋሉም፡፡

ኢትዮጵያዊያን እስላሞች ይሔንን የተሳሳተና እጅግ የተዛባ ለገዛ ሀገርና ሕዝብ ክህደት የተሞላበት አቋም አስተሳሰብ እንዲይዙ ያደረጉት ዓረቦቹ ናቸው፡፡ ዓረቦቹ ከዚህም አልፈው በጃንሆይ ዘመን በወቅቱ ለአፍሪካ ትጫወተው የነበረውን የማይተካ ሚና እንደ መያዣ በመጠቀም በመንግሥታችን ላይ ጫና በማሳደር የእስራኤል ኤምባሲን ዘግተን አምባሳደሯን እንድናባርር ከእስራኤል ጋር ያለንን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችንን እንድናቋርጥ አድርገውም ነበር፡፡ ይታያቹህ**!** ይህ ሁኔታ ምን ያህል የአንዲት ሀገርንና ሕዝብን ሉዓላዊነትና ክብር መዳፈር እንደሆነ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

በደርግ መንግሥት ላይም ተመሳሳይ ጫና ቢደርስበትም ደርግ ከዓረቦቹ ጋር ግልጥ የሆነ የጥላቻ ፖለቲካ ቁርቋስ ውስጥ የነበረበት ሁኔታ ስለነበረ ተጽእኗቸውን ከምንም ባለመቁጠር የተጠናከረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከእስራኤል ጋር ያደርግ ነበር፡፡ ወደ ወያኔ ስንመጣ ወያኔ ዓረቦቹን በመፍራት ከእስራኤል ጋር እጅግ የተቆጠበ ግንኙነት ነው ያለው፡፡ ዓረቦቹ ለወያኔ የማይበጅ ተግባርና ሸፍጥ ፈጽመው ባገኘው ጊዜ ብቻ ለማስፈራራት ያህል ተጀምሮ ወዲያው የሚቋረጥ ግንኙነት ከእስራኤል ጋር ከመፍጠሩ በስተቀር እስከአሁን የተጠናከረና ቀጣይ ግንኙነት ሲፈጥር አልተስተዋለም፡፡ ይህ የሰሞኑን ግንኙነትም ሊመሠርት የቻለው ዓረቦቹ ማለት ሳውዲ ዓረቢያና ኳታር ልዩ ወታደራዊ ስምምነት ከሻአቢያ ጋር በመፈጸም ሠራዊታቸውን አሰብ አስፍረው ወደ ድንበር ሁሉ አስጠግተው ራዳር **(**የበረርት መቆጣጠሪያ**)** በመትከል ለሻአቢያ ተጨማሪ ጉልበት በመሆናቸው በዚህ ምክንያት በተፈጠረበት ቁጣና ኩርፊያ ነው ወደ እስራኤል ያቀናው፡፡

በኔ እምነት እኛ ስለ ዓረቦቹ ብለን ባለፉት ዘመናት ከእስራኤል ጋር ግንኙነታችንን ማቋረጣችን ወይም ማቀዝቀዛችን ዓረቦቹን በሀገራችንና በሕዝቧ ጥቅሞች ላይ ጥቃት ከመፈጸምና ከማድረስ እንዲታቀቡ አድርጓቸው የሚያውቅበት ዘመን ኖሮ አያውቅምና ቀድሞም ሆነ አሁን ዓረቦቹን በመፍራት ከእስራኤል ጋራ ያለንንና የነበረንን ግንኙነት ማቋረጣችንና ማቀዝቀዛችን ትክክለኛ እርምጃ አልነበረም፡፡

ከወያኔ ሰብእናና ማንነት አንጻር ሳየው አሁንም የተመሠረተው አዲስ ግንኙነት ይቀጥላል የሚል እምነት የለኝም፡፡ በዓረቦቹ ቀንደኛ ጠላት ተብለን ተፈርጀን መጠቃቱ ካልቀረልን ግንኙነታችንን ከእስራኤል ጋራ ማጠናከሩ በዓረቦቹ ሊደርስብን የሚችለውን ጉዳት ከመቀነስ ከመከላከልም አኳያ ብልህነት፣ የተሻለ አስተሳሰብና ከሁለት አንድ ያጣ አለመሆን በሆነ ነበር፡፡

ወደ ኢትዮጵያዊያን እስላም ወገኖቻችን ጉዳይ ስመለስ እኔ ይሄ ነገር እንደቀላል ሳይታይ ትኩረት ተሰጥቶት እንደ ሕዝብና ቀደም ሲልም እንደ መንግሥት በአሁኑ ጊዜም መንግሥት የለም እንጅ እንደ መንግሥት ሥራ አለመሠራቱ ፍጹም ትክክል አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደም ከባባድ ዋጋ አስከፍሎናል ወደፊትም ሳያስከፍለን እንደማይቀር የሚያጠራጥር ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

ከዓመታት በፊት ጀምሬ በተለያዩ ጽሑፎቻ ላይ ይህ ጉዳይ ተዛማጅ ጉዳይ ሆኖ በመጣ ቁጥር በተደጋጋሚ ሳላነሣው ቀርቸ አላውቅም፡፡ እስኪ በተለያዩ ጊዜያት ያነሣኋቸውን ከዚህ በታች ያለውን ትንታኔ ተመልከቱና እስላም ወገኖቻችን ከሀገራቸውና ከሕዝባቸው ከማንነታቸው ጥቅም በተጻረረ እጅግ በተሳሳተ አስተሳሰብና ሁኔታ ላይ እንዳሉ ታዘቡ፡- ...እርግጥ ነው በሀገራችን እንደ ወያኔ ሁሉ እጅግ በሚገርም ሁኔታ ጽንፍ የያዘ ፀረ ኢትዮጵያና አልቃይዳዊ ዓላማ አቋምም ይዘው በታወረ ስሜት በመነዳት ቀድሞ ከደርቡሽ ጋር እየተሰለፉ በተደጋጋሚ የገዛ ሀገር ወገናቸውን ሲወጉ ሲያጠፉ የነበሩትንና ሳይሳካላቸው የቀሩትን የአባቶቻቸውን ጅኒና ዓላማ ወርሰው ዛሬም በገዛ ሀገራቸው ሕዝባቸውና ማንነታቸው ላይ በጠላትነት የተሰለፉ፣ ሀገሪቱንና ሕዝቧን ለዓረብ በባርነት አሳልፎ ለመስጠት የሚመኙ የሚቋምጡ፣ የገዛ ማንነታቸውን ጥለው ከቋንቋ አነጋገር እስከ አለባበሳቸው ድረስ ሁለመናቸውን ዓረባዊ ያደረጉ፣ በዐረባዊ ስሜትና ማንነት የተዋጡ፣ እራሳቸውን የሸጡ፣ ስለራሳቸው ማንነት ቅንጣት እንኳን ታክል ዴንታና ቁጭት የሌላቸው ደናቁርት አሸባሪና የዓረብ ባንዶች እስልምናን ከሚከተሉ ወገኖቻችን መሀል ጨርሶ የሉም እያልኩ አይደለም፡፡ በሚገባ አሉ፡፡

እነኝህን ግን ወያኔ በአጋርነት ስለሚመለከታቸው በመሀከላቸው ሌላ የጥቅም ግጭት ካላጋጠመ በስተቀር ወያኔ በእነኝህ ላይ ይዘምታል ብየ አላስብም፡፡ እንደ እነዚህ ዓይነት አጥፊ የእስልምና ተከታይ አካሎች በዚህ ዘመን በሀገራችን እንዳሉ የተረዳሁት በተለያየ አጋጣሚ ከአንዳንድ የእስልምና ተከታዮች ጋር ስነጋገር እንዲህ ዓይነት ሰዎች ከመሀላቸው መኖራቸውን ካረጋገጡልኝ በኋላ ነው፡፡

አጠቃላይ የእስልምናን ገጽታ ከማንነታችን አኳያ በሀገራችን ያለውን ሁኔታ ስናይ ቅኝቱ በፍጹም ትክክል አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ነጥቦችን እናንሣ፡፡ አለባበስን እናስቀድምና ስለ አለባበስ ስናነሣ ተወቃሾቹ ወንዶቹ ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቁምነገሩ ሰውነታቸውና ጸጉራቸው እንዳይታይ በልብስ መከለል ከሆነ ሂጃቡን

የሀገራቸውን ነጠላ ወይም ኩታ ቀሚሳቸውንም የሐበሻ ቀሚስ ማድረግ ሲችሉ ይሄንን ወርውረው በመጣል የሚጠቀሙት ከላይ እስከ ታች የዓረብን ልብስ ነው።

ይሄ ብቻውን አሸባሪነት ነው ለማለት ሳይሆን ለማንነታቸው ያላቸው ግምትና ጥላቻ ይሄንን ያህል ከሆነ ወደዚያ በሚወስደው መንገድ ላይ ናቸው ማለት ነውና ቢጠነቀቁ መልካም ነው ለማለት ነው። ወደዱም ጠሉም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለገዛ ሀገራቸው እሴቶች ጠላቶች ሆነዋል። ቁርአናቸው ከዕይታ መከለል መሸፈን ያለባቸውን የሰውነት አካል እንዲሸፍኑ እንዲከልሉ አዘዘ እንጅ እስልምናን ሲቀበሉ ከልብሳቸው እስከ ቋንቋቸው ሁለነገራቸውን የዓረብ እንዲያደርጉ ጨርሶ አላዘዘምና።

እስልምናን ከሚከተሉ ወገኖቻችን ጋር በተለያየ መንገድ ተወያይቻለሁ። ጥቂት የማይባሉቱ እንዲያውም የሚበዙቱ አንድ ሲሉት የሰማሁት ጉዳይ አለ **"**ሀገር ማንነት ከምትለው ከነፍሳችንም በላይ ነቢያችንንና ሃይማኖታችን እንወዳለን**!** ለእነሱም ነፍሳችንን እስከመስጠት ድረስ ቁርጠኞች ነን**!** በዚህ አንደራደርም**"** የሚል ነው። ልብ በሉ እኔ የምላቸው **"**ባልጠራ ግንዛቤና ከቁርአናቸው ትእዛዝ ውጭ ኢትዮጵያዊ ማንነታቹህን እየሸረሸራቹህና የራሳቹህን ማንነት ጥላቹህ ዓረባዊ እየሆናቹህ ነውና ይሄ ከእስልምና ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር ስለሌለ እስልምናቹህን መከተል ትችላላቹህ ሀገራቹህንና ማንነታቹህን ግን ጠብቁ**!"** ነው የምለው እንጅ እስልምናቹህን ጣሉ አይደለም።

የሚሰጡት ምላሽ ግን አለባበሳቸውን ጨምሮ እምነታቸው ሳያዛቸው የሚከተሉትን ዓረባዊ ባሕል ከእስልምና ጋር እንደማይገናኙ እያወቁ የሚገናኙ አድርገው በመቁጠር **"**ሀገር ማንነት ባሕል የምትለው ነገር አይገባንም ለኛ ነቢያችንና ሃይማኖታችን ይበልጡብናል**!"** በማለት ኃይልና ቁጣ ስድብና ዘለፋ የተሞላበትን ምላሾች ነው የሚሰጡት።

የእነዚህ ወገኖች ችግር እስልምናንና ዓረብነትን፣ እስልምናንና የዓረቦችን ፖለቲካዊ **(**እምነተ አሥተዳደራዊ**)** ኢኮኖሚያዊ **(**ጥሪታዊ**)** ባሕላዊ ጥቅሞችን መለየት አለመቻል ነው። ዓረቦች ሁለንተናዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ሁለቱንም የተለያዩ ነገሮች ቀላቅለው ሲሰብኳቸው ስለኖሩ ይሄ ችግር ሊከሰትባቸው እንደቻለ እገምታለሁ። እስልምናን መቀበል ማለት የዓረብ ባሪያ ሎሌ ባንዳ መሆን ማለት አይደለም። ዓረቦች እንዲጠበቅላቸው የሚፈልጉት የራሳቸው ማንነት እንዳላቸው ሁሉ እኛም ሐበሾች **(**የአቢስ ሕዝብ**)** ከነሱ የተሻለ እንዲጠበቅልን የምንፈልገው ማንነት አለን።

የራስን ጥሎ የዓረብን መያዝ ማለት የውዴታ ባርነት ነው። የገዛ ማንነትን መካድ ነው። ችግሩ ወገኖቻችን ይሄንን አለመረዳታቸው ብቻ ሳይሆን ለመረዳት አለመፈለጋቸውም ነው። እንደ ሕዝብና እንደ መንግሥት ሥራ አልተሠራም የምለው ይሄንን ግንዛቤ ባለመፍጠራችን ነው። የዚህን ጉዳይ አደገኛነት የማይረዳ ሰው የሚኖር አይመስለኝም። እነኝህ ወገኖች በደም ኢትዮጵያዊ መሆናቸውንና በኢትዮጵያዊነታቸውም ዜጋ በመሆናቸው ብቻ ሀገራቸውንና ማንነታቸውን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ጨርሶ መቀበል አይፈልጉም። ዓረቦች በእስልምና ሽፋን የዓረብን ጥቅሞች እንዲጠብቁ እንዳደረጓቸው አያውቁም ማወቅም አይፈልጉም። ዓረቦች ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ወገኖቻችንን ዓረባዊ እያደረጉበት ያለው አኪያሔድ ከቁርአን ውስጥ የሌለና ያልታዘዘ ሊኖርና ሊታዘዝም የማይገባ ሆኖ እያለ የእኛ ወገኖች ዓረባዊ ለመሆን መፍቀዳቸው ነው እጅግ የሚደንቀው።

እንዲህ ዓይነት የተሳሳተና እጅግ የተዛባ አስተሳሰብ አመለካከት ያላቸው ወገኖች ከፊታውራሪ አመዴ ለማ መማር ያለባቸው በርካታ ቁም ነገሮች አሉ፡፡ እንደምታውቋቸው ሁሉ ፊታውራሪ አመዴ ለማ እስላም ናቸው፡፡ ፊታውራሪ አመዴ መካ የሀጂ ጉዞ ከማድረጋቸውና እዚያ ባጋጠማቸው አጋጣሚ የነበራቸውን የተሳሳተ ግንዛቤ ከመጣላቸው በፊት በሳቸው እምነት እስላም መሆን ማለት ከአለባበስ ጀምሮ እስከ ቋንቋ አጠቃላይ ባሕላቸውን ዓረባዊ ማድረግ ይመስላቸው ነበር፡፡

ለሀጂ ጉዞ መካ የተገኙበት አጋጣሚ ይሄንን የተሳሳተ ግንዛቤና አስተሳሰብ ከስሩ ነቅሎ የጣለላቸውን ጠቃሚ ትምህርት ያገኙበት አጋጣሚ ተፈጠረ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- የሐጂ ጉዞ ሥነሥርዓቱ በሚከናወንበት ወቅት ፊታውራሪ አጠገባቸው ካለ አንድ ኢንዶኔዢያዊ እስላም ጋር ይተዋወቃሉ፡፡ በትውውቁ ወቅት ይህ ኢንዶኔዢያዊ ከስሙ ጀምሮ እስከ አለባበሱ ድረስ እንደሳቸው ግንዛቤ የእስላም አልሆነላቸውም፡፡

እናም ግራ ስለገባቸው ጠየቁት "ስምህን ጨምሮ አለባበስህ ግን የእስላም አይደለም!" አሉት፡፡ ሰውየውም መልሶ የእስላም አለባበስና የእስላም ስም ማለት ምንና የቱ እንደሆነ ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም "የእስላም ስምማ መሐመድ፣ ሁሴን፣ ጁሐር፣ ከድጃ፣ ፋጢማ … የእስላም አለባበስ ደግሞ" ብለው የለበሱትን ልብስ እያሳዩ "ይሄ ጀለቢያ… ነው" ሲሉ ገለጹለት፡፡ እዚህ ላይ የባዕድ ስምን የመጠቀም ችግር የእስላም ወገኖቻችን ችግር ብቻ አለመሆኑን ማውሳት እወዳለሁ፡፡ ክርስቲያን ነኝ የሚለው ወገናችንም በተለይም ሠለጠንኩ የሚለው ከተሜው ሃይማኖተኛ የሆነ እየመሰለው የአይሁድን ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ እየፈለፈለ እያወጣ ለልጆቹ መሠየሙት በሰፊው ተያይዞታል፡፡ በተለይም መናፍቃኑ ሥራየ ብለው ይዘውታል፡፡ መዋዕለ ሕፃናት ብትሔዱ ሰምታቹሀቸው የማታውቋቸውን የአይሁድ ስሞች በዓይነት ትቆጥራላቹሀ፡፡

ይህ ኢንዶኔዢያዊ ሰውየ በፊታውራሪ የተሳሳተ አስተሳሰብ በመገረም የጠቀሷቸው ስሞች ዓረብኛና የዓረብ ስሞች እንጅ የእስላም ስሞች አለመሆናቸውን፣ ያሳዩት ልብስም የዓረብ እንጅ የእስልምና አለመሆኑን ዓረቦች እስልምናን ከመቀበላቸው በፊትም ዓረብኛ ቋንቋ ቋንቋቸው እንደመሆኑ እነኝህን ስሞች ይጠቀሙና መጠሪያ ስሞቻቸው የነበሩ መሆኑን፣ አለባበሳቸውም የዓረቦች ባሕላዊ አለባበስ በመሆኑ ጀለቢያን ዓረቦች እስልምናን ከመቀበላቸው በፊት ይጠቀሙበት የነበረ ልብስ መሆኑን በመግለጽ ያሉት ነገር ሁሉ ከዓረቦች ጋር እንጅ ከእስልምና ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑን፣ እስልምናን መቀበል ማለት የራስን ማንነት ባሕል ቋንቋ ወዘተረፈ. ትቶ የዓረብን መቀበል መውረስ ማለት አለመሆኑን፣ እሱ ኢንዶኔዢያዊ እንጅ ዓረብ አለመሆኑን ስለሆነም ማንነቱት ዓረባዊ ማድረግ የማይገባው መሆኑን፣ እስልምናን መቀበል ማለት ሁለነገርን ዓረባዊ ማድረግ ሊሆን ያልቻለበትና ተገቢ ያልሆነበት ምክንያትም ባሕልን ቋንቋን ማንነትን መቀየር ቢቻል የቆዳ ቀለምን ገጽታን ቀይሮ እንደ ዓረቦች ማድረግ የማይቻል በመሆኑ መሆኑን፣ ይሄንን የሚል ትዕዛዝም በቁርአን ውስጥ ፈጽሞ የሌለ መሆኑን፣ እሱ እስልምናን ሲቀበል ከነማንነቱ እንጅ ማንነቱን ጥሎ አለመሆኑን አብራርቶ ገለጸላቸው፡፡

ፊታውራሪም ሰውየው የተናገረው ነገር ሁሉ እውነትና አሳማኝ በመሆኑ ሰውየውን አመስግነው በነበራቸው የተሳሳተ አስተሳሰብ አፍረው ሰውየው የተናገረውን እንዳለ ከመቀበል ውጪ ምንም ያደረጉት ነገር አልነበረም፡፡ ሀገራቸው እንደመጡ ጀለቢያውን አውልቀው ጣሉና (በነገራችን ላይ ቀሚስ ወይም ጀለቢያ የዓረቦች ብቻ ሳይሆን አይሁዶቹን

ጨምሮ ባጠቃላይ የመካከለኛው ምሥራቅ ባሕላዊ ልብስ ነው) ጀለቢያውን ጥለው የሀገራቸውን ባሕላዊ አለባበስ እጀ ጠባባቸውን ለበሱ ኩታቸውንና ካባቸውን ደረቡበት፡፡ ጭራቸውን በጃቸው ያዙ፡፡ በቃ እስኪሞቱ ድረስ አለባበሳቸው ይሄው ነበረ፡፡ ቤታቸው ሲታይ ሙዚየም (ቤተቅርስ) ሊመስል በሚችል መልኩ የሀገራቸውን ታሪካዊ ቅርሶች በሚያሳዩ ሥዕሎችና ቅርጻ ቅርጾች አንቆጠቆጡት፡፡ እስላምነትን በዓረብነት ሳይሆን በሐበሻነት ተቀበሉት ኖረውበትም አለፉ፡፡

"የባሕል ልብሳችንን እማ ሁልጊዜ እንዴት እንጠቀማለን ለበዓል ለበዓል ካልሆነ በስተቀር ሁል ጊዜ የባሕል ልብሳችንን መልበሱ ምቾት አይሰጠኝም" የምንል ካለንም የእነ እከሌ ነው የማይባለውን ገበያ ላይ ያለውን ልብስ ገዝተን ዓለማቀፋዊ አለባበስን መጠቀም ይቻላል፡፡ ልብሱ ሥሪትነቱ የአውሮፓ የአሜሪካ ወይም የጃይና ሊሆን ይችላል፡፡ ሱሪና ሹራቡ እንዲሁም ከላይ የሚለበሱ ልብሶች ሥሪትነታቸው የእነዚህ ሀገራት ይሁን እንጅ የእነሱ ባሕላዊ ልብሶች አይደሉምና ያንን በመጠቀማችን የሌላ ሀገር ባሕላዊ ልብሶችን እንደተጠቀምን በማሰብ ልንሳቀቅ አይገባም፡፡

"እስልምናን የተቀበለ ሁሉ የራሱን ቋንቋ ጥሎ ዓረብኛን ይያዝ" የሚል ትዕዛዝ በቁርአናቸው እንደሌለ እየታወቀ ዓረቦች የባሕል ወረራ ለማድረግ ሲሉ "ዓረብኛ ቁርአን የወረደበት ቅዱስ ቋንቋ ስለሆነ እስላም ለሆነ ሁሉ ዓረብኛን ማወቅ ግዴታው ነው!" እያሉ እየሰበኩ ቋንቋቸውን ያስፋፋሉ፡፡ ከቋንቋቸውም ጋር አብረው ብዙ ነገራቸውን ያስፋፋሉ፡፡

እጅግ የሚያሳዝነው ይህ የዓረቦች አባባል ከዓረብ ውጪ ለሆነው ስድብ መሆኑን ከዓረብ ውጭ ያለው ሌላው እስልምናን ተቀባይ የሰው ዘር አለመረዳቱ ነው፡፡ ለመሆኑ የቋንቋ እርኩስ አለ እንዴ? ከእግዚአብሔር ሌላ ከዓረብኛ ውጪ ያሉ ቋንቋዎችን የፈጠረ ሌላ እርኩስ ፈጣሪ አለ እንዴ? በዓረብኛ ቋንቋ እርኩስ ነገር ሊወራ አይችልም እንዴ?

ይሄንን እያሉ ከሚያታልሉት ዓረቦች ይልቅ ደግሞ ማን ይገርመኛል መሰላቹህ? ይሄንን የዓረቦችን አባባል እውነት አድርገው የተቀበሉ ከዓረብ ውጭ ያሉ ሌሎች እስልምናን የተቀበሉ ዘሮች፡፡ ዓረብኛ ከቁርአን በፊት አልነበረም ወይ? ቁርአን ቋንቋን የሚቀድስ ሆኖ ዓረብኛ ቁርአን ሲወርድበት ወይም ሲጻፍበት ከሆነ የተቀደሰው ሌላውም ቋንቋም ቁርዓን ሲጻፍበት ይቀደሳል ማለት ነውና ቁርአናቹህን በየራሳቹህ ቋንቋዎች አጥኑት፡፡ መሐመድ ቁርአንን በዓረብኛ የጻፈው ግን የሚያውቀውና የራሱ ቋንቋ ዓረብኛ ስለነበረ ነው እንጅ ዓረብኛ ከሌሎች ቋንቋዎች ተለይቶ የተቀደሰ ስለሆነ አይደለም፡፡

ዓረብኛ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ቋንቋዎችንም ማወቁ ይጠቅማል እንጅ አይጎዳምና ቋንቋን ማወቁ መልካም ነው፡፡ ቋንቋውን ማምለኩና የራስን ርኩስ ሌላውን ቅዱስ ማለቱ ግን ችግር ያለበትና እጅግ ያልበሰለ አስተሳሰብ ነው፡፡ "ዓረብኛ ቋንቋ ቋንቋየ ያልሆንኩት እኔ እርኩስ ነኝ!" ብሎ ማለትም ነው ትርጉሙ፡፡ ሰውን የሚቀድሰውም የሚያረክሰውም ሥራው ነው እንጅ ቋንቋ አይደለም፡፡ ሰው ዓረብ ስለሆነ ቅዱስ አይሆንም ሌላ ዘር ስለሆነም እርኩስ አይሆንም፡፡ ማንኛውም ቋንቋ እንደቋንቋነቱ እርኩስ ነገር ሊነገርበት ይችላል ቅዱስ ነገርም ሊነገርበት ይችላል፡፡ የዚህን ያህል አላግባብ የሌሎች ማንነት ምርኮኛ መሆን ፍጹም ተገቢ አይደለም፡፡ ካመናቹህበትና ካስፈለጋቹህ በየራሳቹህ ቋንቋዎች ቁርአኑን ማጥናት ወይም

መቅራት መጸለይ ይኖርባቹሀል እንጅ እስልምናን ለፖለቲካቸው መጠቀሚያ ባደረጉ በብልጣብልጥ ዓረቦች ፖለቲካ ተታላቹህ የዓረብ ማንነት ምርኮኛ ቅጥረኛ ባሪያና ባንዳ ልትሆኑ በፍጹም አይገባም፡፡

እናም ወገኖቸ ሆይ! የቱንም ያህል የኢትዮጵያዊነትን አሻራ እየጣላቹህ የዓረብን ማንነትና አሻራ ብትላበሱት ከጥቁርነታቹህ ከኢትዮጵያዊ ቀለማቹህ ከሐበሻነታቹህ ተቀይራቹህ የዓረብ የቆዳ ቀለም ልትይዙ አትችሉምና ልትለውጡት የማትችሉት ነገር እንዳለባቹህ በማሰብ በማንነት ቀውስ በሽታ እራሳቹህን ባታውኩ ባታሰቃዩ እራሳቹህን ብታከብሩ ለራሳቹህ ዋጋ ብትሰጡ እራሳቹህን መሆን ብትችሉ ለጤናቹህ መልካምና ሰላምም ነው ለማለት እወዳለሁ፡፡

ከዓመታት በፊት ምን ታዘብኩ መሰላቹህ፡- በሸገር ነጋሪተ ወግ (ሬዲዮ) የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (መካነ ትምህርት) የቋንቋ መምህር የሆነ መምህር ደሴ ቀለብና የሙዚቃ (ዘፈን) ባለሙያ የሆነው ሠርጸ ፍሬስብሐት የግእዝ ትምህርት የሚሰጡበትን አንድ ዝግጅት ጀምረው ለአጭር ጊዜም ሲሰጡ ነበር፡፡ ብዙ ሳይቆይ ተቋረጠ፡፡

ለመቋረጡ ምክንያት የሆነው እጅግ በሚገርምና በእውነት ለሰሚው ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ይደረጋል ብሎ ለመገበት የሚያስቸግር ዐይን ያወጣና ትንሽም ሐፍረት የሌለበት ድፍረት በኢትዮጵያዊነታቸው የገዛ ሀብታቸውና እንደ ሁለቱ ዜጎች ሁሉ ይሄንን እሴት የመጠበቅ ጠብቆም ለትውልድ የማውረስ ግዴታ ያለባቸው ሆኖ እያለ የእስልምና ተከታዮች ነን ያሉ እራሳቸውን ለጠላት የቀጠሩ የጠላት ቅጥረኞች "ጣቢያው ለግእዝ የዓየር ሰዓት እንደሰጠ እንደፈቀደ ሁሉ ለእኛም ዓረብኛን የምናስተምርበት የአየር ሰዓት ይሰጠን! ካልሆነ ግን ይህ የግእዝ ትምህርት ዝግጅት ይቋረጥ!" በማለት የነጋሪተ ወግ (ራዲዮ) ጣቢያውን ቀርበው ጠየቁ፡፡

እጅግ የሚገርመው ደግሞ የእነዚህን የዓረብ ቅጥረኛ ባንዳ ኢፍትሐዊና የክህደት የቅጥረኝነት ጠላትነት የተሞላበትን ጥያቄ ይህ የነጋሪተ ወግ ጣቢያ እንዴት አሳማኝና አግባብነት ያለው ጥያቄ ሆኖ እንዳገኘው አላውቅም በጥያቄያቸው መሠረት ያን ዝግጅት እንዲቋረጥ አደረገ፡፡ ግእዝ ቋንቋችንም በገዛ ሀገሩ የመነገር መብቱን አሳጡት፡፡ ዜጎችም በገዛ ሀገራቸው ቋንቋቸውን የመማርና የመጠበቅ መብት እንዲያጡ ተደረገ፡፡

እንደ ኢትዮጵያዊ ግእዝ ቋንቋ እከሌ ከእከሌ ሳይባል ለኢትዮጵያዊያን በሙሉ ሀብታችን፣ ቋንቋችን፣ ቅርሳችን፣ የማንነታችን መገለጫ፣ የሥልጣኔያችን መዝገብ፣ የፍልስፍናችን ልሳን፣ በርካታ ምሥጢሮችን ደብቆ የያዘ ቋንቋችን ነው፡፡ ለኢትዮጵያዊያን ዓረብኛ ቋንቋ ቋንቋችን ነው እንዴ? እንዴት ነው ከግእዝ ጋር እኩል ልናፎካክረው የምንችለው?

የግእዝን ጥቅም ያወቁት ምዕራባዊያን "ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" እንዲሉ የግእዝ ትምህርትን በየ ዩኒቨርስቲያቸው (መካነትምህርታቸው) የግእዝ ትምህርትን በመስጠት ከ **1500** ዓመታት በፊት ጀምሮ እየዘረፉ እየሰረቁ የወሰዷቸውን የብራና መጻሕፍት የያዟቸውን ሁለንተናዊ ዕውቀቶች በማስጠናት በመመራመር ሥልጣኔያቸውን እንዳደራጁ ከራሳቸው አንደበት ሳይቀር ይገለጻል፡፡

እነኝህ የግእዝ ቋንቋ ምንነት የገባቸው ሁለቱ ዜጎች ይሄንን ከሞት አፋፍ ያለ ስንት ነገር ያያዘ ሀብታችንን ባለባቸው ማንነትን እሴታችንን የመጠበቅና ጠብቆም ለትውልድ የማስተላለፍ የዜግነት ግዴታ ይሄንን ሥራ ያለ ማንም

እረዳት በግል ተነሣሽነት እየሠሩ እያለ ነበር በእነዚህ ምን እየሠሩ እንደሆነ ጨርሶ በማያውቁ እብዶች እንዲቋረጥ የተደረገው፡፡ እንግዲህ **"**በሬ ካራጁ**"** እንዲሉ ትክክለኛውን ግንዛቤ ካለመያዝ የተነሣ እምነታችን የሚሉትን እስልምናን ከማንነታቸው ጋር እያጣረሱ በመወናበድ በማንነት ቀውስ ውስጥ ባሉ እንዲህ ዓይነት ኢትዮጵያዊነታቸውን በካዱ ጥፋታችንን በሚመኙ በተቻላቸው መጠንና ባመቻቸው ጊዜም ለዚህ ተግተው እየሠሩ ባሉ የአሸባሪ ጀሌዎች ነው ተከበን ያለነው፡፡

አንዱ አብዱላህ ኢብኑ ኡመር የተባለ ሰው ምን አለኝ መሰላቹህ **"**እየውልህ ወያኔን ከአንተ በላይ አምርረው ከሚጠሉት ውስጥ አንዱ ነኝ። በእምነቴ ጉዳይ ግን ጫፉን እንድታነሣብኝ አልፈልግም። የተቀደሰችውን እና በጌታ ጥበቃ ስር ያለችውን ሀገር ሳውድ አረቢያን ከኢትዩጵያ ጋር እኩል ላይልህ አልችልም። የኢትዮጵያን ባንዲራም ከሳውዲ ባንዲራ ጋር እኩል አድርጌ ላይልህ አልችልም፡፡ በእምነቴ አልደራደርም**!"** አለኝ፡፡

ዐያቹ ህ አይደል የዓረቦቹን የፖለቲካ ሥራ ውጤት**?** አሁን እንዲህ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ወገኖች ምናቸው ነው ኢትዮጵያዊ**?** እነዚህ ሰዎች ይሄንን በማለታቸው በሀገራቸውና በሕዝባቸው ላይ ክህደት እንደፈጸሙና ከሀገር እስከመባረር የሚያደርስ ወንጀል መፈጸማቸውን አያውቁም፡፡ የሀገራችን ሕጎች በሙሉ እነኝህን ሰዎች በዚህ ወንጀላቸው ምክንያት በሀገራችን የተቀመጡ የባዕድ ሀገር ሰላዮች እንደሆኑ አድርጎ ነው የሚመለከታቸው፡፡

የሚያሳስበው ጉዳይ ይሄንን ዓይነት አጥፊ አመለካከት ያላቸው ዜጎቻችን ጥቂት አለመሆናቸው ነው፡፡ ይህ አስተሳሰባቸው የሀገራችንን የዜግነት ሕግ አንድ ዜጋ ወይም ዜግነትን የወሰደ የባዕድ ተወላጅ ለሀገሩ ለኢትዮጵያ ሊያደርግ የሚገባውንና የዜግነት ግዴታውን የሚቃረን የሚተላለፍ የሚዳፈር ወንጀል የሆነ አስተሳሰብ ነው፡፡

ስለሆነም እነኝህ ሰዎች ተለይተው እስከታወቁ ጊዜ ድረስ እኛን መስለው የሀገራችንን ጥቅም እየተጋሩ በሀገሪቱ የመኖር መብት የላቸውምና ወደ ሳውዲ ዓረቢያ መሸኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የሚያሳዝነው የገዛ ሀገራቸውን ከድተው እንሞትላታለን የሚሏት ሳውዲ ዓረቢያም እንኳን ልትቀበላቸው ይቅርና ከነመፈጠራቸውም እንኳ የማታውቃቸው ጭራሽም የሰውነት ክብር የማትሰጣቸው እንደ ውሻና እንደ መርገም ጨርቅም የምትጠየፋቸው መሆናቸው ነው፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ እንዲህ ብለው በማሰባቸው ጤነኞች ናቸው ትላላቹህ**?** እውነት እንነጋገር ከተባለ እንደ ዓረብ እርኩስና ጋኔናም ሕዝብ በዚህች ምድር አለ**???**

እኔ ክርስቲያን ነኝ፡፡ ያውም እኔ እንደ ክርስቲያንነቴ እስላሞቹ ሳውዲ ዓረቢያን ሰው መሆኑን በሚያውቁት **"**መጨረሻ ላይ የተላከ ነቢይ**"** የሚሉት መሐመድና ዘመዶቹ ስለኖረባት ስላስተማረባት ስለረገጣት ብቻ ተቀድሳለች ብለው እንደሚያስቧት እንደ መካና ከመካም ቀጥሎ የመሐመድ ቤተሰቦች ስለረገጡት ስለተሰደዱበት **2**ኛ ቅዱስ ስፍራ **3**ኛ ቅዱስ ስፍራ **4**ኛ ቅዱስ ስፍራ እንደሚሉት ሳይሆን ኢየሩሳሌምን የዓለም መድኃኒት አምላካችን ፈጣሪያችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ያደገባት፣ ተአምሩን ያሳየባት፣ የማዳን ሥራውን የሠራባት፣ በኪደተ እግሩ የባረካት፣ በደሙ ጠብታ የቀደሳት መሆኗን እያወኩና እያመንኩም ነው እስላሞቹ ሳውዲዓረቢያንና ዓረቦቹን በሚያዩበት ዓይን እስራኤልንና እስራኤላዊያንን ከሀገሬ አስበልጬ የማላየው ወይም የማናየው፡፡

አምላክ የማዳን ሥራውን የሠራባት ሀገር መሆኗ ብቻውን ኢየሩሳሌምን ከሀገሬ አስበልጨ ለማየትና ለእሷ መሥዋዕት ለመሆን እስላሞች ለመካ ከሚያቀርቡት ምክንያት የተሻለ ምክንያት ነበረን፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ኢየሩሳሌምን በቅዱስ ሥፍራነቷ እንድናውቃት ከማድረግ በስተቀር እስራኤልንና እስራኤላዊያንን ከሀገራችንና ከሕዝቧ አስበልጠን እንድናይና እንድንሠዋላቸው አላስተማረችንም አልመከረችንም፡፡

ይሄም በመሆኑ የፈለገ ነገር ቢሆን ኢየሩሳሌምን ከኢትዮጵያ ጋር እኩል አድርገን አናያትም፡፡ ለሀገራችን እንደምንሞተውም ለኢየሩሳሌም አንሞትም፡፡ ጌታ በኢየሩሳሌም ይወለድ ይደግ እራሱንም የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ይሠዋባት፤ ከዚህ ከዚህም የተነሣ ትቀደስ እንጅ እሱን ካለመቀበሏ የተነሣም ደግሞ የረገማት ሀገር መሆኗንም እናውቃለንና፡፡ እኔ በገዛ ፈቃዴ ኢየሩሳሌምን እወዳለሁ አፈቅራለሁ እንጅ ጌታ እኔን ክርስቲያን ከሆንክ የግድ ኢየሩሳሌምን ከሀገርህ አስበልጠህ ዕያት ሙትላትም አላለኝምና፡፡ ስሙ እስከከበረባት እስከተቀደሰባት ቅዱስ ሥጋው እስከተቆረሰባት ክቡር ደሙ እስከፈሰሰባት ጊዜ ድረስ ቅንጣት እንኳን ሳታንስ ኢትዮጵያም ከኢየሩሳሌም ጋር በእኩል ደረጃ የተቀደሰች ናትና፡፡ የቀረው የታሪክ ጉዳይ ነው የሚሆነው፡፡

እንግዲህ እኛ ክርስቲያኖቹ እነሱ ለመካ እንደሚሉት ሁሉ በሃይማኖት ምክንያት በጌታ በአምላክ ሃይማኖታዊ የመድኅን ሥራ የተፈጸመበትን ምድር መውደድ ካለብን እንደነሱ በነቢይ ሳይሆን በአምላክ እንደመረገጧ ከእነሱ የተሻለ የጠነከረ ምክንያት እያለን በሃይማኖታችን የተነሣ ከሀገራችን ይልቅ ያንን ምድር እንድንወድ ለዚያ ምድር ዋጋ እንድንከፍል እንዳልተገደድነው ሁሉ እነሱም በተመሳሳይ እንገደዳለን ብለው ሊያስቡ በጭራሽ ባልተገባ ነበር፡፡ እንዲህ ብለው እንዲያስቡ የሚፈልግ የሚገፋፋ የሚሰብካቸው አካል ካለ ይህ አካል የራሱን ጥቅም የሚያስከብር ፖለቲካ እየሠራባቸው እንጅ እምነታቸውን እየሰበካቸው እንዳልሆነ ሊያውቁበት ሊነቁበት ሊጠነቀቁበት ይገባል፡፡

እኔ ይሄንን ነገር ለማመን ከመቸገሬ የተነሣ ሳስበው ሕልም ሕልም ሁሉ ይመስለኛል፡፡ እንዴት ሰው የራሱን ማንነት ጥሎ ለሌላው ምናልባትም ለጠላቱ ማንነት ነፍሴን እሰጣለሁ ይላል? እኔ ክርስቲያን ነኝ ክርስቲያን በመሆኔ ግን ሀገሬንና ከቋንቋየ ጀምሮ እስከ ባሕሌ ድረስ ማንነቴን እንድጠላ እንድንቅ አላደረገኝም፡፡ ክርስትናየን በማንነቴ በቋንቋየ በባሕሌ ኖርኩት አከበርኩት እንጅ፡፡

በእርግጥ ከአውሮፓ የመጣ ክርስትና ነው ብለው ፕሮቴስናንትና ካቶሊክ የሆኑ ወገኖች ለሀገራችንና ለማንነታችን ያላቸው ግምት ከላይ እንደጠቀስኳቸው እስላሞች ነው፡፡ መዝሙሮቻቸውን ጨምሮ እሴቶቻቸው ሁሉ ምዕራባዊ ነው፡፡ የሚያስጠብቁት ጥቅም የሰበኳቸውንና የሚረዷቸውን ምዕራባዊያን ጥቅሞች ነው፡፡ ተግባሮቻቸውም ሁሉ ኢትዮጵያዊነትን በማጥፋት ላይ ያተኮረ በዚህም የተጠመዱ ናቸው፡፡

በእርግጥ የተለያዩ ሀገራት የሀገራችንን ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ኢኮኖሚያዊ (ጥሪታዊ) ታሪካዊና ባሕላዊ ጥቅሞች በማጥፋት የየራሳቸውን ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ኢኮኖሚያዊ (ጥሪታዊ) ታሪካዊና ባሕላዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ሥራ እንደሚሠሩ እንደሚጥሩ ከድሮ ጀምሮ የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም የዚህ ግብግብ ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ወገኖችንና ተግባራቸውን ስናይ ግን እጅግ መገረማችን የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ታዲያ ይህ ሕዝብ እንደሕዝብ መንግሥቱም እንደ መንግሥት በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት የለበትም ትላላቹህ?

ለማንኛውም ሀገርንና ማንነትን በተመለከተ የእኔ ሃይማኖት ግን ከምንም በላይ ሀገሬንና ማንነቴን እንድወድ እንድጠብቅ እንድኮራባት እንድሞትላትም አድርጋ ቀረጸችኝ እንጅ የራሴን አስጥላ ሃይማኖትህ መጣበት የምትለውን ሀገር ጥቅም እንድይዝና የራሴን ጥየ ለነዚያም ጥብቅና እንድቆም እንድጋደል አላደረገችም፡፡

ለነገሩ የኔ ሃይማኖት (በየኪዳኑ ስሟ እየተቀያየረ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተብላ የምትጠራዋ) ከዚህ ወደሌላው የሔዳ የተሰበከች እንጅ ከየትም አልመጣችም፡፡ ከዚህ ቀደም በአንድ ጽሑፌ ላይ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ከነሱ ወደኛ መምጣቱ እርግጥ ሆኖ እስራኤሎችን ከእግዚአብሔር ጋራ ያስተዋወቃቸውን አብርሃምን የባረከው የመልከጼዴቅን ኢትዮጵያዊ መሆን በማንሣት ሃይማኖት ከዚህ ወደዚያ የሔደ እንጅ ከዚያ ወደዚህ ያለመምጣቱን፤ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር አስቀድሞ በዚህች በአንዲቷ ሃይማኖት ውስጥ ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲፈጸሙ ቀጠሮ ይዞላቸው የነበሩና ጊዜያቸው ሲደርስ የተፈጸሙ ኪዳናት ናቸው እንጅ በራሳቸው ሃይማኖት አለመሆናቸውን በማንሣት ሃይማኖታችን ከየትም የመጣ ሳይሆን የእኛ የራሳችን መሆኑን መግለጼ ይታወሳል፡፡ ይህ ወርቃማ ማንነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ሊቆምለት ሊጠብቀው የሚገባ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀብት ማንነትና ቅርስ ነው፡፡

የኔ ሃይማኖት ለዚህች ሀገርና ማንነት ካላት የላቀ ቦታ የተነሣ እንዲያውም ይህች ሀገር የተቀደሰችና ልዑል እግዚአብሔርም ከእናቱ ጀምሮ ዋና ዋና ለሚላቸውና ከፍተኛውን ተጋድሎ ለፈጸሙ ቅዱሳን የዐሥራት ሀገራቸው እንድትሆን የሚሸልማት ብርቅ ድንቅ ቅድስት ሀገር እንደሆነችና ለዚህች ሀገር ነፍሴንም ጨምሮ ምንም የምሰስተው ነገር እንዳይኖር በመምከርና በማስተማር በዜግነቴ ለሀገሬ እንድቆም እንድኮራባት እንጅ ለባዕድ እንድቆም አድርጋ አይደለም ያሳደገችኝ፡፡

ከዚህም የተነሣ ሳይሆን አይቀርም እነዚህ ወገኖች በደም ኢትዮጵያዊያን ሆነው ሳለ የገዛ ሀገራቸውን በመከዳት ለባዕዳን ከዚያም ባለፈ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው እንደ ጠላት ለሚቆጥሯቸው ሀገራትና ሕዝቦች እሴቶችና ማንነት ጥብቅና ሲቆሙና ሲዋደቁ እጅግ እጅግ የሚገርመኝ የሆነው፡፡

አንድ የዓረቦች አባባል ትውስ አለኝ ዓረቦች ምን ይላሉ "በመንገድህ ላይ መርዘኛ እባብና ሐበሽ (ኢትዮጵያዊ) ቢያጋጥሙህ ቀድመህ ሐበሻውን ወይም ኢትዮጵያዊውን ግደለው!" የሚል፡፡ አይገርሟቹህም? ይሄንን ያህል ከእባብም በከፋ መልኩ ለሚጠሏቸውና ለሚጠየፏቸው ሊያጠፏቸውም ሌት ተቀን ለሚያሴሩት ለሚመኙት እኩዮች እንዲህ እንደሚያስቧቸውና እንደሚጠሏቸው እያወቁ እንሞትላቹሀለን ሲሉ? ይሄ የጤና ነው ትላላቹህ? በጣም የሚገርመኝ ደግሞ የተማሩ ፊደል የቆጠሩ ናቸው የሚባሉትም እንዲህ የሚያስቡ መሆናቸውና መጃጃላቸው ነው፡፡ የተማረ ሰው አይመረምርም? አይጠይቅም? የመማር ፋይዳው ታዲያ ምንድን ነው?

እንደምታውቁት አሁን በዚህ ወቅት ሁሉም ባይሆኑም የሚበዙቱ በተሟሟቀ ሁኔታ ከዚህ ብዥታ ጋር ሆነው ለእስልምና እየታገሉ እየመሰላቸው ለዓረብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ ጥቅሞች እየታገሉ ያሉ እስልምናን የሚከተሉ ወገኖች አሉ ዋጋም እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡ አደጋው ያለው እዚህ ላይ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ዓረቦች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ይህችን ሀገርና ሕዝቧን በተመለከተ የተለየ ፍላጎት ይዘው በሀገራችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ባሕላዊ ጥቅሞች ጉዳይ ላይ እጃቸውን እያስገቡ የራሳቸውን ጫና ሲፈጥሩ፤ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ታሪካዊና ባሕላዊ ጥቅሞች ለማስጠበቅ አውዳሚ ጦርነቶችን ከማድረግ ጀምሮ ብዙ ነገር ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ዛሬም ላይ ዓረቦች እንደወትሮው ሁሉ በዚህች ሀገር ላይ ላላቸው ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) ኢኮኖሚያዊ (ጥሪታዊ) ታሪካዊና ባሕላዊ ጥቅም በሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት ጫናና ፍልሚያ አጋጣሚው ባመቻቸው ጊዜ ሁሉ እጃቸውን በሚያስገቡበት ወቅት እንደ ጥንቱ ሁሉ እነኝህ ወገኖች መጠቀሚያ መሆናቸው የማይቀርና ግልጽ ጉዳይ ነው፡፡ ይሄ ከባድ አደጋ ነው፡፡ ስለሆነም ከባድ ሥራ ይጠበቅብናል፡፡

በእርግጥ ፊት ለፊት ወጥተው ከወያኔ ጋር እየተጋፈጡ ያሉት ወገኖች ቁጥር ያን ያህል ላቅ ያለ ላይሆን ይችላል፡፡ ከጀርባ ግን በሚሊዮኖች (አእላፋት) የሚቆጠሩ የዓላማ ተጋሪ እንዳላቸው የሚጠረጠር አይመስለኝም፡፡ የሚያሳዝነው የእነሱ ትግል ግብ የሀገርንና የሕዝብን ክብር ሉዓላዊነት ታሪክ ባሕል ማንነት እሴቶችን ሁሉ በተመለለከተ ቢሳካላቸው ከወያኔ በከፋ መልኩ የከፋ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን አለመታወቁ ነው፡፡ ይሄንን አብዛኞቻቸው በቅጡ ሳያውቁት የሚያደርጉትን ደግሞ ሌላው ኢትዮጵያዊ የማይፈልገው የማይፈቅደውም ከመሆኑ የተነሣ የጥቅምና የዓላማ ግጭት መነሣቱ የማይቀር ይሆናል፡፡ በዚህ መሀል የጠላት እርስ በእርስ እያፋጀ ሀገሪቱን የማዳከም ሰትራቴጂ (ስልት) ተሳክቶላቸው እንደቆየው ሁሉ ወደፊትም ይሳካላቸው ይሆናል፡፡

የሚገርመው የብዙኃን መገናኛዎቹም አጥብቀው የሚሠሩት እስላሞቹ ዓረባዊ እንዲሆኑ ነው፡፡ በበዓላቶቻቸው የሚያዘፍኑላቸው ዘፈኖች የዓረብ ዘፈኖችን ነው፡፡ ቆይ ግን የኛ የክርስቲያን በዓላት ሲሆን የራሳችንን ሀገራዊ ዘፈኖችን ነው እንጅ የእስራኤል ዘፈን ይጫወትልናል እንዴ? እኛስ ይሄን እንድታደርጉ ፈልገን እናውቃለን እንዴ! እኛም ሐበሻ እነሱም ሐበሻ እንደመሆናቸው ማንነታችንን የመጠበቅ ግዴታ አለብንና ለምን በሀገራቸው ሀገራዊ ዘፈኖች በዓላቶቻቸውን አታከብሩላቸውም? ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የንግድ ባንኮችን ማስታወቂያዎች የተመለከታቹህ እንደሆነ "ለእስልምና ተከታዮች" በሚል ከወለድ ነጻ ነገር ግን ባንኮቹ በገንዘባቸው ሠርተውበት የሚያገኙትን ትርፍ ሊጋሩ የሚችሉበትንና አስቀድሞ እንደ ተንቀሳቃሽ ሒሳብ ያሉ በአማርኛ ሲሰጧቸው የነበሩትን የባንክ አገልግሎቶች ወደ ዓረብኛ ለውጠው ዋዲያማና፣ ቀርድ፣ ኢጃራህ፣ ሙሽራካ፣ ኢስቲስናህ ወዘተ. እያሉ "እንግሊዝኛው በከለን ኸረ እየተረነምን በእኛ በራሳችን ቋንቋ እንጠቀም" እያልን በምንወቀቅስበት ወቅት አሁን ደግሞ ጭራሽ ሌላም ጨምረው ዐረፉት፡፡

አገልግሎቶቹ የአማርኛ ሥያሜ ስለሌላቸው ነው እንዳይባል መተርጎሙና መሠየሙ አልቸገረ በዚህም ላይ አስቀድሞ ሲሰጥ የቆየ አገልግሎትንም ነው ወደ ዓረብኛ የመለሱት፡፡ እኔ የሚገርመኝ እነዚህ ወገኖች እኮ ዓረቦች አይደሉም፡፡ የራሳቸው ቋንቋ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡ ምናለ ቅርባቸው በሆነው በሚገባቸው በገዛ ቋንቋቸው ሁሉም በሚረዱት ብታስተናግዷቸው?

የብዙኃን መገናኛው በበዓታቶቻቸው በሚያቀርቡት ዘፈኖች ባንኮችም በሚሰጧቸው አገልግሎቶች እነኝህ የእስልምን ተከታይ ወገኖቻችን ለምን በግድ ዓረባዊ ስሜት እንዲሰማቸው ይደረጋል? ለምን ወደ ባዕድ ይገፋሉ? ለምን ባዕድነት እንዲሰማቸው ይደረጋል? ለምን አላግባብ ዓረባዊ ተጽእኖ እንዲጫናቸው ይደረዳል? ሃይማኖት ሌላ ማንነት ሌላ ጉዳይ ሆነው እያለ ሊቀላቀሉ በማይገባ ጉዳይ ላይ ለምን ትቀላቅሏቸዋላቹህ? እባካቹህ እያሰባቹህ እያገናዘባቹህ ሥሩ?

ለማንነት ተጠንቀቁ? ወለድ መቀበል እስልምና የሚከለክል ቢሆንም ይህንና ሌሎች የባንክ አገልግሎቶች የሚገለጽበት ቋንቋ ጉዳይ ግን ከእስልምና ጋራ የሚያገናኘው ጉዳይ የለምና ኃላፊነት እንደሚሰማው እንደ ተማረ እንደ ባለ አእምሮ ዜጋ አስቡና ምን ለማን በምን ቋንቋ እንደሚባል ተረድታቹህ ሥሩ?

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሃይማኖትና በዘር ሳንለያይ ለጠላቶቻችን ሳይሆን ለእኛ የምትሆን ነጻ እኩልነት የሰፈነባትን ኢትዮጵያን ለማምጣት ስንል የማይቀርልንንና የሚገጥመንን ፈተና በብቃት ተወጥተን ዓላማና ግባችንን ለማሳካት ታጥቆ መዘጋጀቱ ግድ መሆኑን ልንረዳ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ረገድ የገባቸውና ፈተናው ተግዳሮቱ አጋጣሚውን ለመጠቀም ጠላት ሃይማኖትንና ዘርን ሽፋን አድርጎ እንደሚመጣ በመረዳት በሀገራቸውና በሕዝባቸው ጥቅሞች ላይ ፈጽሞ ያለመደራደር ጠንካራ አቋም የያዙ የእስልምና ተከታይ ወገኖቻችን እነኝህን የሳቱና ያልገባቸውን የጠላት መጠቀሚያ ወገኖቻችንን ከያዙት የጥፋት ዓላማ እንዲመለሱና ለገዛ ሀገራቸውና ለሕዝባቸው ዋጋ መሥዋዕትነትን እንዲከፍሉ የመምከርና የማስተማር ዓረቦች የራሳቸውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እስልምናን ሽፋን አድርገው ከጋቷቸው እጅግ የተሳሳተና ሀገራቸውን ከሚጎዳ ግንዛቤ ነጻ እንዲሆኑ እስልምናቸውን በማንነታቸው እንዲኖሩት የማድረግ ተግባራቸውን ሳይደክሙና ሳይሰለቹ ጠንክረው እንዲወጡ በዚህ አጋጣሚ አበክሬ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com